# ሊምፍ ኖድ ማውጣት/ማስወገድ
## Lymph Node Removal


*Image: National Cancer Institute*

ሊምፍ (Lymph) ማለት በተፈጥሮ ሰውነት ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ፈሳሽ ነው። በሰውነት ውስጥ በመዘዋወር ቆሻሽን የሚያጣራ ብሩህ የሆነ ንጥረ ፈሳሽ ነው። ይህንንም ነጥረ ፈሳሽ በሰውነት ውስጥ እንዲዘዋወር የሚረዱት ማጣሪያ ወንፊት ያላቸው ልምፍ ኖዶች (Lymph node) ይባላሉ። እነዚህ ልምፍ ኖዶች በሰውነት ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑትን እንደ ካንሰር ህዋሳትንና ሚክሮቦችን በማጣሪያቸው አጥምደው በመያዝ ከሰውነት ውስጥ እንዲወገዱ ያደርጋሉ።

የሴቶች የጡት ካንሰር ከነዚህ ሊምፍ ኖዶች ጋር የተገናኘ ሊሆን ይችላል። ኖድ-ገብ (Node-positive) ማለት በነዚህ ሊምፍ ኖዶች ውስጥ የካንሰር ሕዋሳት አለ ማለት ነው። ኖድ- አልባ (Node negative) ማለት በነዚህ ሊምፍ ኖዶች ውስጥ ከካንሰር ነፃ ናቸው ማለት ነው። ካንሰሩ በሊምፍ ኖዶቹ ውስጥ መኖርና አለመኖሩን ማወቅ ለሐኪምሽ በምን ዐይነት ዘዴ ማከም እንዳለበት ለመወሰን ይረዳዋል።

የሊምፍ ኖዶች ዋና ስራቸው ለስውነት የማይጠቅሙና ፀረ-ሰውነት የሆኑ እንደካንሰር የመሳሰሉትን ሕዋሳት አጣርቶ ማስወገድ ነው። ስለዚህ ከዋናው የካንሰር እጢ በማምለጥ ወደ ሌላ አካል ክፍሎች የሚዘዋወሩት እነዚህን የካብሰር ሕዋሳትን ለማጥመድና ለመመርመር ካስፈለገ ኖዶቹን መመርመር
ነው ።
ስለዚህ ካንሰር ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል እንዳይዛመትና መልሶ እንዳያድግ እነዚህን ካንሰራማ ልምፍ ኖዶች ማስወገድ አስፈላጊ ነው።

ሊምፍ ኖድ ባዮፕሲ (Lymph node biopsy) ይህ ማለት የቀዶ ጥገና አሰራር ሲሆን ጥቂት የሊምፍ ኖዶችን ቆርጦ በማውጣት ካንሰር እንዳላቸውና እንደሌላቸው የሚደረግ የሕክምና ዘዴ ነው። ከጡት አጠገብ ካለው ብብት ሥር ተቆርጠው የወጡትን ሊምፍ ኖዶች ሐኪሙ በማጉያ መነፅር በማዬት ካንሰራማ ሕዋሳት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ይመረምራል። ካንሰራማ የሆኑት የሊምፍ ኖዶች መብዛት የካንሰሩ ይዘት ምን ያህል አስጊ መሆኑን ያመለክታል።

ሐኪምሽ አስር ሊምፍ ኖዶችን ቆርጦ ካወጣ በምርመራው ጊዜ ስለካንሰሩ በቂ መረጃ ያገኛል። የቀዶ ጥገና ሐኪምሽ እንዲሁ ካንሰራማ መስለው የታዩትን ኖዶች ቆርጦ ያወጣቸዋል። ምን ያህል ሊምፍ ኖዶች መወገድ እንዳለባቸው የሚወስነው የሰውነትሽ አቅምና የቀዶ ጥገናው ሐኪም ችሎታና እውቀት ነው። እያንዳንዱ ሴት በቁጥር የተለያዩ ሊምፍ ኖዶች በብብቷ ሥር አላት፡።አንዳንዶቹ በተፈጥሮ አምስት ብቻ ሲኖራቸው ሌሎቹ ግን ከሰላሳ በላይ ሊኖራቸው ይችላል።

ሊምፍዴማ (Lymph edema) ይህ በጡት አኳያ ባለው እጅ ላይ በካንሰሩ ምክንያት የሚፈጠር እብጠት ነው። ሊምፍዴማ ሊሆንባቸው የሚችሉት ከ 5% — 10% ፐርሰንት ባሉ በሽተኞች ላይ ነው። ብዙ ሊምፍ ኖዶችን ያስወጡና ከቀዶ ጥገናው በኋላ ጨረርና ኪሞቴራፒ ለሚሰጣቸው ሴቶች አደጋው በ25% ፐርሰንት ከፍ ያለ ነው።

ሊምፍዴማ (Lymphedema) ማለት በካንሰር በተመረዘው ጡት አኳያ ያለው እጅ ሲያብጥ ነው። የሊምፍዴማ ሁኔታ ሊፈጠር የሚችለው ከ5% — 10% ፐርሰንት በሆኑ የካንሰር በሽተኞች መሐል ነው። ብዙ ሊምፍ ኖዶችን ያስወጡ እንደዚሁም ቀዶ ጥገና የተደረገላቸውና ጨረራ (Radiation) ኪሞቴራፒ (Chemotheraphy) የተሰጣቸው ሴቶች የጉዳቱ መጠን ከ25% ፐርሰንት ከፍ ያለ ነው። እንዲሁም ጊዜ በሻረውና ባረጀው ራዲካል ማስቴክቶሚ ማለትም በጡት አካባቢ ያሉትን ጠቅላላ የሊምፍ ኖዶችን ማስወገድ እንዲሁም ሙሉ ጡቱንና የጡቱን ጡንቻዎች ቆርጦ በማውጣት ሕክምና ላደረጉ ሴቶች የሊምፍዴማ (Lymphedema) መጠን የጉዳቱ መጠን በ25% ፐርሰንት አካባቢ ነው።

ወደሌላ የሰውነት ክፍሎችና ወይም ከጡት ተነስተው ወደ ደም ስርጭት ውስጥ የተቀላቀሉትን የካንሰር ሕዋሳት ለመዋጋት የሊምፍ ኖዶችን ቆርጦ ማውጣት የካንሰር ሕዋሳትን ለመዋጋት አማራጭ የሌለው ነው። ስለዚህም እነዚህ ወደ ሌላ የሰውነት ክፍል ያመለጡትን የካንሰር ሕዋሳት ለማጥፋት ሌላ የተለየ የሕክምና ዘዴ መጠቀም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው።

# የሴንቲነል ሊምፍ ኖድን ማውጣት
## Sentinel Lymph Node Removal




*© 2005 Terese Winslow, U.S. Govt. has certain rights*

በሴንቲነል ሊምፍ ኖድ ቀዶ ጥገና ተቆርጠው የሚወጡት ጥቂት ሊምፍ ኖዶች ብቻ ናቸው። ባሁኑ ወቅት ይህ አሰራር ዘዴ ተቀባይና ተግባራዊ ሆኖ ተገኝቷል። ሴቶች መጀመሪያ የጡት ካንሰር ሲጀምራቸው የልምፍኖዶቹ የካንሰር ህዋሳት መጠንና አደጋ አነስተኛ በሆነበት ወቅት የሴንትነል ሊምፍኖድ ባዮፕሲ መውሰዱ በጣም አስፈላጊ ነው። ነገር ግን በካንሰር በጣም የታወከ ከሆነ የሴንቲነልን ሊምፍ ኖድ ሕክምና ሴቶች እንደአማራጭ አድርገው መጠቀም የለባቸውም።

በእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት (dictionary) ሴንቴነል (sentinel) እንደ ዘበኛ፣ እንደ ተናካሽ ውሻ እንዲሁም ተከላካይ እንደሆነ ያበስራል። በዚህም አንጻር ለጡትሽ በአንደኛ ደረጃ በተከላካይነት ወይም በዘበኛነት የሚቆመው ሴንቲነል ሊምፍ ኖድ (sentinel lymph node) ነው። በዚህም የሴንቲነል ሊምፍ ኖድ ቀዶ ማስወገድ ወቅት የቀዶ ጥገናው ሐኪሙ የሚመለከተው በካንሰሩ ከመረቀዘው የጡት አካባቢ ፈሳሹን እያጣራ የሚወሰደውን የመጀመሪያውን ሊምፍ ኖድ ነው። የካንሰር ሕዋሳት በጡቱ ውስጥ ያለውን የካንሰሩን እጢ እየለቀቁ ወደ ሌላ አካባቢ ሊጓዙ የሚችሉት ከሌሎች ልምፍ ኖዶች ይልቅ በሴንቲነል (sentinel) ሊምፍ ኖድ አማካኝነት ነው።

የሴንቲነል (sentinel) ሊምፍ ኖድ ማስወገድ ሊታሰብ የሚችለው በነዚህ በመሳሰሉት ምክንያቶች ነው። አስር ወይም ካስር በላይ ሊምፍ ኖዶችን ከማስወገድ እንዲሁም እያንዳንዱን ካንሰር እንዳላቸውና እንደሌላቸው ከማጥናት ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ ጥቂት ካንሰር ሊኖርባቸው የሚችሉትን ሊምፍ ኖዶች ማስወገድ አማራጭ ስለሚሆን ነው። የሴንቲነል ሊምፍ ኖድ ካንሰር ከሌለው የሚያሳየው ሌሎችም ኖዶች ካንሰር ሊኖርባቸው እንደማይችል ያስገነዝባል። የቀዶ ጥገናው ሐኪም ምንጊዜም የሴንቲነልን ሊምፍኖድና በተጨማሪም ሁለት ወይም ሶስት ኖዶችን ቆርጦ ለምርመራ ያወጣል።

በጣም ትንሽ የጡት ካንሰር ያለባቸው ሴቶች ማለትም ከሁለት ሴንቲሜትር ያልበለጠና ከቀዶ ጥገና በፊት ሊምፍ ኖዶቹ የተመረዙ መስለው የማይሰሙ፣ ከብብት ስር አንዱን ወይም ጥቂቶቹን አውጥቶ በመመርመር በሊምፍ ኖዶቹ ውስጥ ያለው የካንሰር ይዘት በእርገጥ እንዴት እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል። የአምስት ዓመታት ጥናት ተደርጎ እንደታየው የሴንቲነል ኖድ (sentinel node) የወጣላቸው ሴቶች ሌሎች ብዙ የሊምፍ ኖዶች ከወጣላቸው ሴቶች እኩል ከካንሰር ነፃ በመሆንና በሕይወት ሊኖሩ እንደሚችሉ ታይቷል።